ልደታ ካቶሊክ ካቴድራል ት/ቤት ሚያዝያ 19 / 2012 ዓ.ም
የትምህርት ዓይነት አካባቢ ሳይንስ
3ኛ ክፍለ ጊዜ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የትምህርት
መካካሻ ጥያቄዎች
ክፍል 1ኛ

ምዕራፍ አራት

. በዙሪያችን የሚገኙ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች

ሀ. አየር ለ. ውሃ ሐ. አፈር

ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ባሕሪያት

- አይመገቡም
- አያድጉም
- እራሳቸውን ችለው ከቦታ ቦታ አይንቀሳቀሱም
- አይተነፍሱም
- አምሳያቸውን አይተኩም . . . የመሳሰሉ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ባሕሪያት ናቸው ::

የአየር ጥቅም

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ለመኖር አየር አየር ያስፈልጋቸዋል :: በተጨማሪም ሕይወት ለሌላቸው ነገሮች አየር ያስፈልጋቸዋል ::

ምሳሌ - ለመኪና ጎማ

- ለፊኛ
- ለኳስ . . . ለመሳሰሉት ያስፈልጋል ::

ማስታወሻ :- በገጽ 89 ላይ ያሉትን ተግባራዊ ክንውን በመሞከር አየር መኖሩን አረጋግጡ ::

መልመጃ

እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ

_______ 1. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ይመገባሉ ::
_______ 2. የመኪና ጎማ ለመሔድ በአየር መሞላት አለበት
_______ 3. አየር የሚያስፈልገው ሕይወት ላላቸው ነገሮች ብቻ ነው ::
_______ 4. እፅዋት አየር ያስፈልጋቸዋል ::
_______ 5. የሰው ልጅ ያለ አየር መኖር ይችላል ::

ለ/ ባዶ ቦታውን በተስማሚ ቃላት ሙላ

1. ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ባሕሪያት ውስጥ ቢያንስ ሶስቱን ጻፍ

____

____

____

የውሃ መገኛ

የውሃመገኛዎች ብዙ ናቸው ። እነርሱም

- ምንጭ
- ሐይቅ
- ኩሬ
- ከጉድጓድ
- ቧንቧ
- ውቅያኖስ
- ወንዝ
- ባሕር
- ዝናብ . . . .

* ዝናብ ዋና የውሃ መገኛ ነው ።

የውሃ ጥቅም

- ለመጠጥ
- ንፅሕናን ለመጠበቅ
- ምግብ ለመዘጋጀት
- እፅዋትን ለማብቀል
- ቤት ለመስራት
- የኤሌትሪክ ሀይል ለማመንጨት
- ለመጓጓዣ
- ለመዝናናት

መስታወሻ:- ከገጽ 91 - 93 ላይ ያሉትን ስዕላዊ መግለጫዎች ተመልከቱ

መልመጃ

ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል መርጠሕ ጻፍ

________ 1. በዙሪያችን የሚገኝ ሕይወት የሌለው ነገር ነው ።
ሀ. እንስሳት ለ. እፅዋት ሐ. ውሃ

________ 2. ዋና የውሃ መገኛ ነው
ሀ. ዝናብ ለ. ሀይቅ ሐ. ወንዝ

________ 3. የመኪና ጎማ የሚሞላው
ሀ. በውሃ ለ. በአየር ሐ. በአፈር

________ 4. ከውሃ ጥቅሞች ውስጥ አንዱ ነው
ሀ. ቤትን ለመስራት ለ. ምግብን ለማዘጋጀት ሐ. ሁለቱም

________ 5. የኮቪድ 19 መተላለፊያ መንገድ ነው
ሀ. መጨባበጥ ለ. እርቀትን ጠብቆ አለመጓዝ ሐ. ሁለቱም

ትእዛዝ ሁለት

6. የውሃ መገኛዎችን በስዕል አሳዩ / ሳሉ / ስዕሉን ከሳላችሁ በሀላ ስዕላዊ መግለጫ ይጻፍበት

መስታወሻ፡- ይህ ወረቀት ግንቦት 3 ተመላሽ ሆኖ በመምህራን ይታረማል ።